አባ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ታኅሣሥ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፤**

ከሁሉ አስቀድሞ በሀገራችን በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የምትኖሩ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ካህናት ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ሁሉ አምላካችን እግዚአብሔር በሕይወትና በሰላም ጠብቆ እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ ።

**«ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ = ምስጋና ለእግዚአብሔር በሰማያት ፣ ሰላም በምድር ፣ ለሰው ልጅም በጎ ፈቃድ ይሁን»** ። /ሉቃ 2 ፥ 14/ ።

ይህ ኃይለ ቃል የሰላም አምላክ ለዓለማችን ሰላምን ለመስጠት ሰው ሁኖ ሲገለጥ ፣ በልደቱ ሰላም የተሰበከላቸው ሰዎችና መላእክት በኅብረት የዘመሩት መዝሙር ነው ። በዚህ ውስጥ ሦስት ነገሮች ተወስተዋል ። የመጀመርያው ልጁን ለሰጠን ለእግዚአብሔር በሰማይ ምስጋና እንደሚገባው ። ሁለተኛ በክርስቶስ ልደት ለምድራችን ሰላም መስጠቱን ። ሦስተኛ በተገኘው ሰላም ተጠቃሚ ለመሆንና በተወለደው መድኃኒት ለመዳን የሰው ፈቃደኛነት አስፈላጊ መሆኑ ናቸው ።
የእግዚአብሔር ልጅ ከሰማየ ሰማያት የወረደውና ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ሰላምን ለዚህ ለዓለም ለመስጠት ነው ። ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስም አስቀድሞ ስለ ወልድ ሰው መሆን ሲናገር «ሕፃን ተወልደ ለነ ፣ ወልድ ተውህበ ለነ = ሕፃን ተወለደልን ፣ ወልድም ለኩነተ ሥጋ ተሰጠልን» ካለ በኋላ «ወይሰመይ ስሙ... ወመልአከ ሰላም» ብሎ የሰላም መገኛ መሆኑን አረጋግጦ ተናግሮ ነበር ። /ኢሳ9 ፥ 6-8/ ።

አምስት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ አድንህአለሁ ብሎ ለአዳም በሰጠው ተስፋ መሠረት ፣ ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከቅድስት ድንግል ማርያምም ተወለደ ። /ገላ 4 ፥ 4/ ።
በሰውና በእግዚአብሔር ፣ በሰውና በሰው ፣ በመላእክትና በሰው መካከል ፣ በኃጢአት ምክንያት ሰላም ጠፍቶ ስለ ነበር ፣ የሰላም ጌታ በቤተ ልሔም ተወልዶ ሰላምን ለሰው ለልጆች ሁሉ ሰበከ ። «ብኪ ድኅነ ዓለም ወበወልድኪ ኮነ ሰላም» እንዳለ ሊቁ ፣ እመቤታችንም መድኃኒታችን ኢየሱስን በመውለዷ ዓለም ዳነ ፤ በልጇም ሰላም ሆነ ። በመሆኑም አምላከ ሰላም ሥጋ ለብሶ ሲገለጥ በልደቱ «ወሰላም በምድር» የሚለው መዝሙር ተዘመረ ።

ጌታችንም በትምህርቱ ለደቀ መዛሙርቱ «ሰላሜን እሰጣችኋለሁ» ብሏቸዋል ። /ዮሐ 14 ፥ 7/። ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲልካቸውም “ወደምትገቡበት ቤት ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ» ነው ያላቸው ። /ሉቃ 10 ፥ 5/
በትንሣኤው ጊዜም በዝግ ቤት ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» ነበር ያላቸው /ዮሐ 20 ፥ 19/ ።
የጥልንና የልዩነትን መንፈስ በፈሰሰው ደሙ ስላስወገደው ሐዋርያው ቅዱስ ጳወሎስ «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ» በመስቀሉ ጥልን ገድሎ ሰላምን አደረገ ብሏል ። በመሆኑም በቤተ ልሔም በሥጋ ሰብእ የተወለደው ጌታ «የሰላም አምላክ» ነው ። /ቈላ 3 ፥ 15 ፤ ሮሜ 15 ፥ 33/ ።

ብርሃነ ልደቱን ለማየት የታደላችሁ በመላው ዓለም የምትገኙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ! ዛሬም የእግዚአብሔር ቃል «የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይብዛ ፣ እርስ በርሳችሁ በሰላም ኑሩ» በማለት ሁላችንንም ይመክረናል ። /ሮሜ 12 ፥ 18/ ።

ሰላም በዓለማችን እጅግ ተፈላጊ በመሆኑ ሁሉም ስለ ሰላም ይናገራል ይጽፋል ። ነገር ግን የሰው ልጅ ለሰላም መጥፋት ምክንያት የሆነውን ነገር ለማስተካከልና ሰላምንም ሀብት ለማድረግ የሚያስችለውን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ የሰላም ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም ። ለዚህ ነው «ሥምረቱ ለሰብእ ፤ የሰው መልካም ፈቃድ» ያስፈልጋል የተባለው ። ሰው ሰላምን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነ እግዚአብሔር ሰላምን ሰጥቷል ፤ ሰውን የሚለያየው ክፉ ነገር ሁሉ በልጁ ሰው መሆን ተወግዷል ፤ ስለሆነም በሕዝብና በአሕዛብ ፣ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ልዩነት በጌታችን ሰው መሆን ተወግዶ ፣ ሰላም

ፍቅርና አንድነት ስለታወጀ «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት» እያልን እግዚአብሔርን ከመላእክት ጋር ልናመሰግን ይገባናል ።

በሥግው ቃል ሰላም ለምድራችን ስለ ተሰበከ «ወሰላም በምድር ፤ ሰላምም ለምድር ይሁን» እያልን ሰላምን እንሰብካለን ። ነገር ግን የዚህ ሁሉ ማሰሪያ በሰላም ለመጠቀምም ሆነ ላለመጠቀም መብቱ የሰው ልጅ ነው ። በመሆኑም በሰላም ለመኖር የሰው ልጅ በጎ ፈቃድ ያስፈልጋልና «ሥምረቱ ለሰብእ ፤ የሰው በጎ ፈቃድ ይሁን» እያልን ሰውን ሁሉ ራሱን ለሰላም እንዲያዘጋጅ ፣ በበክርስቶስ ሰላምም እንዲኖር፣ በሰላም አምላክ ስም ሰላምንና ፍቅርን እንጋብዘዋለን ።
ዛሬ የሰላም ሐዋርያ የሆነችው እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለ ኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት ወደ እግዚአብሔር በምትማፀንበት ወቅት የክርስቶስን ልደት ስናከብር ሁሉም ለሰላምና ለአንድነት ራሱን አዘጋጅቶ የመላእክትንና የኖሎትን መዝሙር «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ» እያለ ሊዘምር ይገባዋል ። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ሰላም ቢሰጠውም ፈቃደኛ ካልሆነ የሰላም ተጠቃሚ ላይሆን ይችላል ። ስለዚህ ለሰላም ራስን ማዘጋጀት የሁሉም ሰው ድርሻ ነው ።

የክርስቶስን ልደት በምናከብርበት በዚህ ወቅት በመላው ዓለም የምትኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ ስለ አገራችን ኢትዮጵያና ስለ ሕዝቦቿ ሰላምና አንድነት የምታዝኑበትና የምትጸልዩበት ጊዜ መሆኑ ይታወቃል ። እኛም የዘወትር ጸሎታችና የውስጣችን ጩኸት እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን ጸሎት እንዲሰማና ኢትዮጵያን እዲታረቃት ነው ። እናንተም ተግታችሁ ሳታቋርጡ በጸሎት ወደ እግአብሔር እንድታመለክቱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።

ክርስቶስ የተወለደው የታሰሩንትንና የተጠቁትን ነጻ ሊያወጣ ፥ የሰውን ባሕርይ ሊያከብርና ከፍ ሊያደርግ ነው ። በዚህ ዕለት የታሰሩትን ፣ የሚጠቁትን ፣ የሚራቡትን ፣ የሚሰደዱትን እያሰብን ልደቱን ልናከብር ይገባል ። ቤተ ሰቦቻቸው የሞቱባቸውን ማሰብ ይገባል ። ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች ፣ ልጆችቸውንም ላጡ ወላጆች በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ልናሰባቸው ይገባል ።

እግዚአብሔር አገራችንን ኢትዮጵያን ይባርክ !

እግዚአብሔር ዓለማችንን በበረከተ ልደቱ ይባርክ ይቀድስ አሜን ።

«ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ፥ ወሰላም በምድር ፥ ሥምረቱ ለሰብእ»

አባ መርቆሬዎስ ፓትርያሪክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

Abba Merkorios

Patriarch of Ethiopia

15521Orchard Drive Bowie MD 20715 Phone:(301) 262-3031